## ከአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት)

## የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ

### አንድነት ችግሮቹን በወቅቱ በመፍታት ጥንካሬውን ያረጋግጣል

አንድ ፓርቲ ዓላማውንና መርሆዎቹን ካስቀመጠ በኋላ እነዚህን ተግባራዊ ለማድረግ እቅድና ስትራቴጂ ይቀይሳል:: አፈፃፀሙን ይከታተላል:: ውጤቱን ይገመግማል:: ግምገማው በእቅድ በተያዘ ሂደት ወይም ወቅቱ በጠየቀበት ጊዜ ሊሆን ይችላል:: በአንድነት የዘጠኝ ወር እድሜ ውስጥ ብሔራዊ ምክር ቤቱም ሆነ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው የፓርቲውን አካሄድ በተመለከተ በርካታ ውይይቶችን አካሂዷል::

በቅርቡ የተወሰኑ የብሔራዊ ምክር ቤት አባላት አንድነት ጤናማና ጠንካራ መሆን አለበት ከሚል እምነት በመነሳት በፓርቲው አካላት አሠራርና በአካላትና በአባላት ግንኙነት አሉ ያሏቸው ችግሮችን በመጠቆም ውይይት እንዲካሄድ ለብሔራዊ ምክር ቤቱ በጽሑፍ ጥያቄ አቀረቡ:: ብሔራዊ ምክር ቤቱም የጽሁፉን ይዘት በስብሰባ ከመረመረ በኋላ የተጠቆሙትን ችግሮች በጥንቃቄ መርምሮና አጣርቶ የሚያቀርብ አምስት አባላት የሚገኙበት ኮሚቴ ሰየመ:: ኮሚቴውም የቀረቡ ችግሮችን ባህሪ በዝርዝር የመረመረና የውሳኔ ሃሳቦችን ያካተተ ሪፖርት ለምክር ቤቱ አቀረበ::

ብሔራዊ ምክር ቤቱም ግንቦት 8 እና 9፣ 2001 ዓም በአደረገው የሁለት ሙሉ ቀን ስብሰባ ቀደም ሲል በተወሰኑ አባላት በቀረበው ችግር ጠቋሚ ሰነድና በአጣሪ ኮሚቴው በቀረበው ሪፖርት ላይ በመመሥረት ዝርዝር፣ ግልጽና ነፃ ውይይት አካሄደ:: በውይይቱ ሂደት አሉ የተባሉ ችግሮች ሁሉ በጥንቃቄ ተዳስሰዋል:: በዳሰሳው ሂደት ጉዳዮችን ከተለያየ አቅጣጫ ለማየትና ትክክለኛ አቋም ላይ ለመድረስ ሲባል ጠንካራ ክርክሮች በቀና መንፈስ ተካሂደዋል:: መፍትሔዎች ተቀምጠዋል:: መፍትሔዎቹ ተግባራዊ የሚሆንባቸው የክትትል ስልቶችና መመሪያዎችም ተሰጥተዋል::

የቀረበው ችግር ጠቋሚ ሠነድ የአንድነት አካላትና አባላት አሠራራቸውንና በመካከላቸው ያለውን የግንኙነት ሁኔታ ቆም ብለው እንዲመረምሩና ጥንካሬና ድክመታቸውን እንዲለዩ፣ ለችግሮቻቸውም አፋጣኝ መፍትሔ ፈልገው ተግባራዊ ለማድረግ እንዲነሳሱ ጥሩ ምክንያት ሆኗል::

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት) ማዕከላዊ ጽ/ቤት UNITY FOR DEMOCRACY AND JUSTICE PARTY (UDJ)

አንድነት ለጥንካሬው፤ ለአላማው መሳካት፤ በአካላትና በአባላት መካከል ለአለው ጤናማ ግንኙነት መዳበር ሲባል ሥርዓት ይዘው በቃልም ሆነ በጽሑፍ የሚቀርቡ ገንቢ ሃሳቦችን ያስተናግዳል:: ለተግባራዊነታቸው ተግቶ ይሠራል::

ለሁለት ቀናት የተካሄደው ውይይት የአንድነት አደረጃጀትና አሠራርን በግልጽነትና በነፃነት ለመመርመር ከማስቻሉም በላይ በአካላቱና በአባላቱ መካከል የበለጠ የመቀራረብ፤ የመግባባትና ይበልጥ የጠነከረ የዓላማ አንድነት መንፈስን ፈጥሯል:: የድርጅቱ የሕዝብ ዓላማ የማሳካት አቅምን ይልበልጥ ለማጠናከር የዚህ ዓይነት ውይይት እንዳስፈላጊነቱ ይቀጥላል::

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት)
ግንቦት 11 ቀን 2001 ዓም
<u>አዲስ አበባ</u>

(አንድነት)
ማዕከላዊ
ጽ/ቤት
UNITY FOR DEMOCRACY AND JUSTICE PARTY (UDJ)